# ተማሪዎችን በቤት ውስጥ መደገፍ ቅድመ-አጸደ ሕፃናት

*በመጀመሪያ በሃዋርድ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የተዘጋጀ እና ለዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ*

## አጭር መግለጫ

ይህ መመሪያ ት/ቤቶች በCOVID-19 ምክንያት በተዘጉበት ወቅት ተማሪዎች በትምህርት ተግባሮች ላይ እንዲቆዩ ለማድረግ ሀሳቦችን እንዲሰጥ የተዘጋጀ ነው። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባራት ልጆቻችን በቤታቸው በሚውሉበት ጊዜ በአዕምሯቸው ንቁ ሆነው እንዲቆዩ ለመርዳት የታሰቡ ናቸው። የተግባር ሀሳቦቹ በት/ቤቶች የሚሰጠውን የመጀመሪያ ደረጃ የመማር-ማስተማር ሂደትን አይወክሉም። የመጀመሪያ ደረጃ የመማር-ማስተማር ምርጥ ተሞክሮዎች ተማሪዎች ወደ ት/ቤት በሚመለሱበት ጊዜ የሚታዩ ናቸው።

ልጆች በቤታቸው የሚያከናውኗቸው ተግባሮችና ሥራዎች እንደምዘና አገልግሎት የሚውሉ ወይም ወደ ተማሪዎች ውጤቶች (ግሬድስ) የሚቆጠሩ አይሆኑም። ቤተሰቦች ዝርዝሩን አንብበው ጠቃሚና ተደራሽ የሆኑ አማራጮችን መምረጥ ይኖርባቸዋል። ተግባራቱ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሠሩ ይችላሉ።

## ምሳሌያዊ የየዕለት ጊዜ ሰሌዳ

| | | |
|---|---|---|
| 8:00-9:00 | **መንቃት እና መዘጋጀት** | ቁርስ መብላት፣ መልበስ እና ለቀኑ መዘጋጀት |
| 9:00-10:00 | **የትምህርት ሰዓት** | ከዚህ በታች ካለው ዝርዝር ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ አማራጮችን ምረጡ። |
| 10:00-10:30 | **ነፃ ምርጫ** | እንደ ሌጎስ፣ ስዕል፣ ምግብ ማብሰል፣ ፐዝሎች፣ የቦርድ ላይ ጨዋታዎች ያለ ተግባርን ምረጡ። |
| 10:30-11:00 | **የስክሪን (የቲቪና ሞባይል) ጊዜ** | ከዚህ በታች ካለው የስክሪን-ተኮር ተግባሮች ዝርዝር ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ምረጡ። |
| 11:00-12:00 | **ምሣ እና ነፃ ጊዜ** | ምሣ ብሉ፣ ለእግር መንገድ ወይም ውጪ ለመጫዎት ሂዱ |
| 12:00-1:00 | **የትምህርት ሰዓት** | ከዚህ በታች ካለው ዝርዝር ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ አማራጮችን ምረጡ። |
| 1:00-1:30 | **ነፃ ምርጫ** | እንደ ሌጎስ፣ ስዕል፣ ምግብ ማብሰል፣ ፐዝሎች፣ የቦርድ ላይ ጨዋታዎች ያለ ተግባርን ምረጡ። |

| | | |
|---|---|---|
| 1:30-2:00 | **ንባብ** | አንድ መጽሐፍ ማንበብ ወይም ከዚህ በታች ካሉት አቅርቦቶች አንድ የኦንላይን መጽሐፍን ምረጡና አንብቡ። |
| 2:30-2:00 | **የከቤት ውጭ ጊዜ** | ለእግር መንገድ ወይም ውጭ ለመጫዎት ሂዱ |
| 2:30-3:00 | **የስክሪን (የቲቪና ሞባይል) ጊዜ** | ከዚህ በታች ካሉት የስክሪን-ተኮር ተግባሮች ዝርዝሮች ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ መምረጥ። |
| 3:00-4:00 | **ነፃ ምርጫ** | እንደ ሌጎስ፣ ስዕል፣ ምግብ ማብሰል፣ ፐዝሎች፣ የቦርድ ላይ ጨዋታዎች ያለ ተግባርን ምረጡ። |

# የትምህርታዊ ተግባር ምርጫዎች

እያንዳንዱ የትምህርት ዘርፍ “የምርጫ ቦርድ” አማራጮች አሉት። በእያንዳንዱ ቀን ከተወሰኑ የትምህርት ዘርፎች የተለያዩ ተግባራትን ለመምረጥ ሞክሩ። እነዚህ አማራጮች የአካላዊ እንቅስቃሴ፣ የመጽሐፍት ንባብ፣ እና የቴክኖሎጅ ጠቀሜታ፣ የመስመር-ላይ አቅርቦቶችን/ግብዓቶችን እና የቴሌቪዥን ፕሮግራም ዕድሎችን ያካትታሉ። ልጆችዎ ስለሚሠሯቸው ተግባራት ከልጆችዎ ጋር መነጋገር የንግግር ክህሎቶቻቸውን እና ግንዛቤያቸውን ለማጠናከር ይረዳል።

ልጆችዎ በየቀኑ የተለያዩ ተግባራትን እንዲመርጡ እና በሁሉም የትምህርት ዘርፎች ቀጣይነትን ለማበረታታት የሚከተለውን ሠንጠረዥ ተጠቀሙ (ከሃዋርድ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የተገኘ እና ለዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ)፦

| ርዕስ | አማራጭ 1 | አማራጭ 2 | አማራጭ 3 | አማራጭ 4 |
|---|---|---|---|---|
| **ቋንቋ እና ሊትረሲ** | በየቀኑ መጽሐፎችን በየቀኑ አንብቡ፣ ወይም ከዴንቨር ካውንቲ የሕዝብ ቤተ-መጽሐፍት ታሪኮችን ለማግኘት ሞባይልን ተጠቀሙ። | በማግኔቶች ስማችሁን ጻፉ። በተመሳሳይ ፊደል የሚጀምሩ እቃዎችን ፈልጉና አግኙ። ከስማችሁ ጋር የሚገጥሙ ቃላቶችን ጻፉ/ፍጠሩ። በቤተሰቦቻችሁ አባላት ስሞች ድገሟቸው። | ስማችሁን እና የቤተሰባችሁን አባላት ስሞች መጻፍ ተለማመዱ። የሚዛመዱ ስዕሎችን ሳሉ። ስዕሎቹን አብራችሁ የምታነቡት ወደ አንድ ታሪክ ለውጧቸው። | ከቤተሰባችሁ ጋር ዘፈኖችን ዝፈኑ። የቃል እና የድምጽ ጨዋታዎችን ተጫወቱ። አስቂኝ ትርጉም/ድምጸት ያላቸው ቃላትን ፍጠሩ። |
| **ሒሳብ** | ወደ ቅርጾች አደን ውጡ። ስንት ቅርጾችን ታገኛላችሁ? ክቦችን፣ ሦስት ማእዘኖችን፣ ካሬዎችን | በቤቱ ውስጥ ያሉ ነገሮችን ቁጠሩ። በእራት ጊዜ ስንት ሰሃኖች አሏችሁ? በመሳቢያችሁ ውስጥ ስንት | እንደ ካልሲዎች፣ ሲቲከሮች እና አሻንጉሊቶች ያሉ ነገሮችን በምድብ በምድብ አስቀምጧቸው። | በአሻንጉሊት ብሎኬቶች፣ ሌጎዎች ወይም ባዶ ካርቶኖች ግንባታቸውን ገንቡ። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | እና አራት ማእዘኖችን ለመፈለግ ሞክሩ። ከዚያም ሞላሌዎችን፣ ኩቦችን እና ፒራሚዶችን ፈልጉ። | ካልሲዎች አሏችሁ? ስንት ቱዲ ቤሮች አሏችሁ? | በእያንዳንዱ ምድብ ያሉትን ነገሮች ቁጠሩ። የትኛው ምድብ ብዙ የትኛው ትንሽ ነገሮች አሉት? | መጠናቸውን አወዳድሩ። የገነባችሁት ማማ ምን ያህል ይረዝማል? የገነባችሁት ማማ ምን ያህል ይሰፋል? ማማችሁን ስላችሁ አሳዩ። |
| **ሳይንስ** | የቤት የሳይንስ መዋዕል (ጆርናል) አዘጋጁ! በእያንዳንዱ ቀን በጽሑፍ ወይም በስዕል መዋዕልን አክሉ። ምን አስገረማችሁ? ምን ታዘባችሁ (አያችሁ፣ ሰማችሁ፣ ተሰማችሁ)? | በቤት ውስጥ የቤት እንስሳ (ፔት) አላችሁ? ከቤት ውጪ አንዳች እንስሳትን ታያላችሁ? የእንስሳ አሻንጉሊት አላችሁ? በቻላችሁት ጥልቀት ምን እየሠሩ እንደሆኑ የሚገልጽ ስዕል ሳሉ። | ምክንያትና ውጤቱን አስቡት። አንድን ኳስ በቀስታ ብትገፉት (ብታንከባልሉት) ምን የሚሆን ይመስላችኋል? አንድን ኳስ በኃይል ብትገፉት፣ ሌላ ምን አሻንጉሊቶችን በተለያዩ መንገዶች መግፋት ወይም መጎተት ትችላላችሁ? | ለማሰስ ወይም ለመፈተሽ የስሜት ሕዋሳችሁን ተጠቀሙ። በቤታችሁ ውስጥ ምን ነገሮች ለስላሳ፣ ምን ሸካራ እና ምን ልሙጥ ናቸው? ምን መራራ፣ ምን ጣፋጭ፣ ምን ከምጣጣ ጣዕም አለው? ምን ነገሮች ከፍተኛ ድምጽን ይፈጥራሉ? ምን ነገሮች ለስለስ ያለ ወይም ዝቅተኛ ድምጽን ይፈጥራሉ? |
| **ሶሻል ስተዲስ** | የቤተሰብ ፎቶዎችን ተመልከቱ እና ስለሰዎቹና በታዎቹ አውሩ። በታዎቹን ግለጹ። እንዴት ከቤታችሁ ጋር ይመሳሰላል ወይም ይለያያል? | በቤት ውስጥ የሚሠሩ ቀላል የቤት ውስጥ ሥራዎች እና ተግባሮች ዝርዝርን አዘጋጁ። የምታደርጉን ነገር ጻፉት። ሥራዎቹ እንዴት እንደሚሠሩ ለሌላ ሰው ማስተማር ትችላላችሁ? | በየቀኑ አዲስ የቦርድ ጨዋታን ተጫወቱ። መከተል ያለባችሁ ሕጎች ምንድን ናቸው? ጨዋታዎቹ እንዴት ይመሳሰላሉ ወይም ይለያያሉ? የእናንተ ተወዳጅ ጨዋታ ምንድን ነው? | በማኅበረሰቡ ውስጥ ስላሉ የተለያዩ ሥራዎች አውሩ እና አንብቡ። እነዚያ ሥራዎች ሰዎችን እንዴት ነው የሚጠቅሟቸው? እናንተ ምን ሥራ ነው ለመሥራት የምትመኙት? ለምን? |
| **የአካላዊ ደህንነት እና የነርቮች እድገት** | ፍራፍሬዎችን እና ቅጠላቅጠሎችን በየዓይነታቸው ለዩ። ከቤተሰባችሁ እና ጓደኞቻችሁ ጋር የምትጋሩት ጤናማ መቆያ (ስናክ) በመሥራት አግዙ። | መያዝ/መቅለብ፣ መዝለል እና ፊደሎችን "ትሬስ" በማድረግ የዓይን-እጅ ቅንጅትን ገንቡ። | ትልልቅ ጡንቻዎችን ለመገንባት የሚረዱ:- በእግር መሄድ፣ ዘለል ዘለል ማለት፣ እምባጥ ማለት፣ መሮጥ፣ በእግር እጣቶች መሄድ ያሉ እንቅስቃሴዎችን አድርጉ። እንደምትወዷቸው እንስሳዎች ያሉ እንቅስቃሴዎችን ተለማመዱ። | ትንንሽ ጥንቻዎች እንዲያድጉ የሚረዱ:- ስዕል መሳል፣ ቀለም ቅብ መሳል፣ መቀሰችን መጠቀም፣ ሸክላ ጭቃ መገንባት ያሉ እንቅስቃሴዎችን አድርጉ። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ረቂቅ ሥነ-ጥበባት** | ምትን ለመፍጠር የቤት ውስጥ እቃዎችን ተጠቀሙ። ዘፈን ፍጠሩ። ጮክ ያሉ እና ለስለስ ያሉ ድምጾችን ተጫወቱ። | የበረዶ ቀብ (ice paint) ለመሥራት ውኃን፣ የምግብ ቀለምን፣ የ“popsicle” እንጨቶችን እና የበረዶ መሥሪያ እቃን (ice molds) ተጠቀሙ። ለጓደኞቻችሁ እና ለቤተሰባችሁ የቀለም ቅብ ስዕሎችን ሳሉ። | የተለያዩ ዓይነት ሙዚቃዎችን (ለምሳሌ፣ ፖፕ፣ ሂፖፕ፣ አገረኛ፣ ክላሲካል፣ አር ኤንድ ቢ).እያዳመጣችሁ ደንሱ። በየቀኑ የተለየ ስታይልን ምረጡ። | አልባሳትን በመልበስ የምትወዱትን ታሪክ ተወኑ። ወይም የምትወዷቸውን ታሪኮች እንዲጫወቱላችሁ አሻንጉሊቶች ሠርታችሁ ተጠቀሙ። |

# ዲጅታዊ መረጃዎች

*በዲጅታዊ መንገድ ሊገኙ የሚችሉ የተወሰኑ ግብዓቶች እዚህ ይገኛሉ፦*

- Scholastic Learn at Home
- PBSKids
- የዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች ዲጂታዊ ቤተመጽሐፍት
- የዴንቨር የሕዝብ ቤተመጽሐፍት ታሪኮችንና ዘፈኖችን በስልክ በእንግሊዝኛ፣ በስፓኒሽኛ፣ በአማርኛ እና በቬትናምኛ የሚገኝ አገልግሎት
- የDPS' አካዳሚክ ቴክኖሎጂ ዝርዝር፡
    - የትምህርት ቤት ዝርዝሮችን (Breakdowns) → የእናንተን ት/ቤት → ሂድ ምረጡ!
    - “የወላጆች ስምምነት ያስፈልጋል” ትር፦ ግብዓቶች በወላጅ ስምምነት አማካኝነት በት/ቤታችሁ ይፈቀዳሉ
    - “የወላጆች ስምምነት ይጠየቃል” ትር፦ በዲስትሪክት የተፈቀዱ ግብዓቶች

## ለስፓኒሽኛ ተናጋሪ ወላጆች የተግባር ሀሳቦች

- Las Provincias
- Bebesymas
- Sapos Y Princesas

## ትምህርታዊ ቴቪ

PBS የተለያዩ ትምህርታዊ ቴቪ ቻናሎች አሉት። በዴንቨር አካባቢ PBSን መጠቀም የምትችሉት እንዲህ ነው።

- በአንቴና
    - Rocky Mountain PBS፦ ቻናል 6.1

- RMPBS KIDS፡- ቻናል **6.2**

- <u>በኬብል ቴቪ (ኮምካስት)</u>
    - Rocky Mountain PBS፡- ቻናል **6 እና 658**
    - RMPBS KIDS፡- ቻናል **245**
    - Create/World*፡- ቻናል **248**
    - በጥያቄ፡- ቻናል **1** ("የእርስዎ ኮሎራዶ")
- <u>ሳተላይት (DIRECTV)</u>
    - Rocky Mountain PBS፡- ቻናል **6**
- <u>ሳተላይት (ዲሽ ኔትዎርክ)</u>
    - Rocky Mountain PBS HD: ቻናል **6**